# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ

# የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ አወሳሰንና እና ሽግግር መመሪያ

# ቁጥር 73/2014

## መግቢያ

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ በከተማና ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ላይ ተመስርቶ የራሱ የሆነ ስትራቴጂ እና የድጋፍ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶለት ላለፉት ዓመታት በዕድገት ተኮር ዘርፎች ላይ በማተኮር በኢንተርፕራይዞች ልማት ላይ አበረታች ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

በ□ህም መሠረት በከተማችን ውስጥ የሚገኙ ስራ ፈላጊ ነዋሪዎችን በመለየት አስፈላጊውን ስልጠና ማመቻቸት ማደራጀት የፋይናስ አቅርቦት የመስሪያ ቦታ እና የገበያ ትስስር ድጋፎች እንዲያገኙ በማድረግ ሰፊ የስራ ዕድል እንዲፈጠር እና በሃገራችን የሚታየውን ስራ አጥነትና ድህነት በመቀነስ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል::

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ ኢንተርፕራይዞች እንደየ ዕድገት ደረጃቸው ድጋፍ የሚሰጣቸው በመሆኑ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፎች ለመስጠት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የድጋፍ ማዕቀፎች በማዘጋጀት ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በዚሁ መሰረትም የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ አወሳሰንና ሽግግር አፈጻጸም መመሪያ የወጣ ቢሆንም በአፈጻጸሙ ላይ ያልተመለሱና ያልተፈቱ ችግሮች በመኖራቸው፣ ኢንተርፕራይዞችን ፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍል እንዲያገኙ ያላደረገ እና ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው ሥርዓት ያላካተተ ሆኖ በመገኘቱ፤

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (3)(ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የዕድገት ደረጃ አወሳሰን እና ሽግግር መመሪያ ቁጥር 73/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

**የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-**

1. **"ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፤የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞች ጨምሮ እስከ 5 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ እስከ ብር 50,000.00 /ሃምሳ ሺ/ ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ እስከ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺ/ ድረስ የሆነ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡
2. **"አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፤ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,001.00 /ሃምሳ ሺ አንድ/ እስከ ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺ/ ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,001.00 /አንድ መቶ ሺህ አንድ/ እስከ ብር 1,500,000.00 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ/ ድረስ ያለ ኢንተርፕራይዝ ነው::
3. **"የኢንተርፕራይዝ ደረጃ ሽግግር"** ማለት አንድ የኢንተርፕራይዝ በዕድገት ደረጃው የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ላይ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ሆኖ ወደ ቀጣይ የዕድገት ደረጃ የሽግግር መስፈርቶቹን በማሟላት መሸጋገር ሲችል ነው::
4. **"የምሥረታ ወይም ጀማሪ ደረጃ"** ማለት አንድ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝን ለመመሥረት ፍላጎት ያላቸው ነዋሪዎች በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ተደራጅተው ሕጋዊ ሰውነት በማግኘት የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ተግባር የሚጀምሩበት ነው::
5. **"የታዳጊ ወይም መስፋፋት ደረጃ"** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ላይ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ሲሆንና ትርፋማነቱ ቀጣይነት ሲኖረው ነው:: በዚህ ደረጃ ያለ ኢንተርፕራይዝ በምሥረታ ደረጃ ከነበረው ቀጥሮ የሚያሠራው የሰው ኃይል ቁጥርና የጠቅላላ ሃብት መጠን ዕድገት ያለው ነው፡፡

6. **“የመብቃት ደረጃ”** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ የገበያ ድርሻውን ለማሳደግ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በሥራ ላይ ካዋለና ለዘርፉ የተቀመጠውን ትርጓሜ መስፈርት ሲያሟላና ወደ ታዳጊ መካከለኛ ሲሸጋገር ወይም በአለበት ደረጃ ጥቃቅን ወይም አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በመሆን በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ የሚቀጥል ሲሆን ነው::
7. **“ታዳጊ መካከለኛ ደረጃ”** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ በመሆን ለታዳጊ መካከለኛ ደረጃ የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት ወደ ኩባንያ ደረጃ የተሸጋገረ የኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ነው::
8. **“ቋሚ የሥራ ዕድል”** ማለት በማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ውስጥ የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ ከአንድ ዓመት ያላነሰ ጊዜ ተቀጣሪ በመሆን በደመወዝ ክፍያ ሰነድ የተረጋገጠ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ነው::
9. **“ጊዜያዊ የሥራ ዕድል”** ማለት በማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ውስጥ ከአንድ ዓመት ያነሰ ጊዜ ክፍያ በማግኘት ጊዜያዊ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ነው::
10. **“ነባር ኢንተርፕራይዝ”** ማለት ህጋዊ ሰውነት ወይም ፈቃድ አግኝተው አንድ ዓመት እና በላይ የሞላቸው ሆነው የተሟላ ወይም በከፊል የድጋፍ አገልግሎት ያገኘ ነው፡፡
11. **“አዲስ ኢንተርፕራይዝ”** ማለት በኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት መሠረት ህጋዊ ፈቃድ አግኝተው ወደ ሥራ ከተሰማሩ አንድ ዓመት ያልሞላው ነው፡፡
12. **“ኢንተርፕሪነርሺፕ”** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ በተሰማራበት ስራ ዘርፍ ገበያ ለማግኘት የህብረተሰቡን የምርትና የአገልግሎት አቅርቦት ፍላጎት በመለየት እንዲሁም ተወዳዳሪዎችንና የገበያ ድርሻቸውን በመለየት ስለ አዋጪነቱ መተማመን ደረጃ ሲደርስ ወደ ምርትና አገልግሎት ስራ የመሰማራት ክህሎት ነው::
13. **“የገበያ ትስስር”** ማለት ለአንድ ኢንተርፕራይዝ የገበያ ዕድል ለመፍጠር ከመንግስት ተቋማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በሀገር ውስጥና ውጪ ከሚገኙ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በግብዓት፣ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት በጎንዮሽና በተዋረድ ግንኙነት የሚፈጠር የግብይት ወይም የሥራ ትስስር ነው::
14. **“ጠቅላላ ሃብት”** ማለት የአንድ ኢንተርፕራይዝ የተከፈለ እና በብድር የተገኘ ሃብት ነው::
15. **“የተጣራ ካፒታል”** ማለት የአንድ ኢንተርፕራይዝ ጠቅላላ ሃብት ሲቀነስ ዕዳ ነው:
16. **“የምርት ወይም የአገልግሎት ማስተዋወቂያ ዘዴዎች”** ማለት ምርትን ወይም አገልግሎትን ለማስተዋወቅ የመገናኛ ብዙሃን፣ ንግድ ትርዒትና ባዛር፣ በራሪ ወረቀት፣ ቢዝነስ ካርድ፣ ቋሚ የማስታወቂያ ቦርድ፣ ካታሎግ፣ ዳይሬክተሪ፣ የኢንተርፕራይዞችን

ስም የያዙ ስጦታዎች እስኪቢርቶ፣ ቁልፍ መያዣ፣ ማስታወሻ ደብተር፣ ፖስት ካርድ፣ እና ድረ-ገጽ ነው፡፡

17. "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
18. በዚህ መመሪያ ውስጥ **በወንድ** ፆታ የተገለፀው **የሴትንም** ፆታ ያካትታል፡፡

**3. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ፣ በስሩ ባሉት ተቋማት እና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**4. የመመሪያው ዓላማ**

የኢንተርፕራዞች የዕድገት ደረጃ አወሳሰንና ሽግግር የአሰራር ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆንና የዕድገት ደረጃቸውን መሰረት ያደረጉ ድጋፎችን መስጠት፤

**5. የመመሪያው አስፈላጊነት**

1. የኢንተርፕራዞች የዕድገት ደረጃ አወሳሰንና ሽግግር ወጥነት ባለውና አሳታፊ በሆነ መንገድ በመረጃ ተደግፎ ለመወሰን፣
2. የሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎች የዕድገት ደረጃን መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ለማስቻል፣
3. ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ሥርዓት ለማስፈን፣
4. በነባሩ የአሰራር ሥርዓቶች ክፍተቶችን በመለየት እና በማሻሻል የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ፤

**6. የመመሪያው መርሆዎች**

1. ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች የሚሰጡ ድጋፎች የዕድገት ደረጃቸውን መሰረት ያደረገ መሆኑንና ተደራሽነታቸውን ማረጋገጥ፤
2. የሚሰጡ ድጋፎች በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲሰጡ ማድረግ፤
3. የሚሰጡ ድጋፎች የኢንተርፕራይዞችን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ማድረግ፤
4. የመንግስት ድጋፍ አሰጣጥ ፍትሃዊ፤ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ሥርዓት መዘርጋት፤

5. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል ያሉበትን ደረጃ ማሳወቅ፤

6. የሚሰጡ የመንግስት ድጋፎች ለማን፣ መቼ፣ እንዴት እንደሚሰጥ ግልጽ ማድረግ በማስፈለጉ፤

## ክፍል ሁለት

## የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ አወሳሰንና እና ሽግግር

7. **አዲስ ለሚደራጁ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ አወሳሰን፡-**

   1. ህጋዊ ሰውነት በማግኘት ወደ ዘርፉ የተቀላቀለ ኢንተርፕራይዝ የያዘውን የሰው ሃይልና የካፒታል መጠን መሰረት በማድረግ በአደረጃጀቱ እና በኢንተርፕራይዝ ዓይነት ተለይቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቃቅን ጀማሪ ወይም አነስተኛ ጀማሪ የዕድገት ደረጃ መሰጠት አለበት፣

   2. አንድ ኢንተርፕራይዝ ጥቃቅን ጀማሪ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ለማግኘት በኢንዱስትሪ ዘርፍ የካፒታል መጠን ከብር 50,000.00 /ሃምሳ ሺ/ ያልበለጠ እና የሰው ሃይሉ እራሱንና ቤተሰብን ጨምሮ እስከ 5 ሰው የቀጠረ መሆን አለበት፡፡

   3. አንድ ኢንተርፕራይዝ ጥቃቅን ጀማሪ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ለማግኘት በአገልግሎት ዘርፍ የካፒታል መጠን ከብር 40,000.00 (አርባ ሺ) ያልበለጠ እና የሰው ሃይሉ እስከ 5 ሰው መሆን አለበት፡፡

   4. አንድ ኢንተርፕራይዝ አነስተኛ ጀማሪ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ለማግኘት በኢንዱስትሪ ዘርፍ የካፒታል መጠን ከብር 100,001.00 /አንድ መቶ ሺ አንድ/ ያላነሰ እና የሰው ሃይሉ እራሱንና ቤተሰብን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰው የቀጠረ መሆን አለበት፡፡

   5. አንድ ኢንተርፕራይዝ አነስተኛ ጀማሪ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ለማግኘት በአገልግሎት ዘርፍ የካፒታል መጠን ከብር 50,001.00 /ሃምሳ ሺ አንድ/ ያላነሰ እና የሰው ሃይሉ እራሱንና ቤተሰብን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰው የቀጠረ መሆን አለበት፡፡

   6. አንድ ኢንተርፕራይዝ ጥቃቅን ወይም አነስተኛ ጀማሪ የዕድገት ደረጃ ለማግኘት የሰው ሃይል ብዛትና የካፒታል መጠን የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ በካፒታል መጠን የሚወሰን መሆን አለበት፡፡

8. የነባር ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ እድሳት፣ ሽግግርና የቆይታ ጊዜ

1. አንድ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ማሳደስና ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ የዕድገት ደረጃ መሸጋገር የሚችለው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ መሆን አለበት፡፡
2. ለኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ እድሳትና ሽግግር የሚሰራው ከሐምሌ 1 እስከ ጥቅምት 30 ድረስ ብቻ ነው፡፡ ይሁንና የዕድገት ደረጃውን መታደስ ባለበት ወቅት ከሃምሌ 1 እስከ ጥቅምት 30 ድረስ እድሳት ያላደረገ ኢንተርፕራይዝ፡-
   ሀ. ከህዳር 1 እስከ 30 የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የዕድገት ደረጃው እንዲታደስለት መደረግ አለበት፡፡
   ለ. በተሰጠው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ካላሳደሰ የዕድገት ደረጃው ተሰርዞ ከድጋፍ ማዕቀፎች ውጪ መደረግ አለበት፡፡
   ሐ. ለኢንተርፕራይዝ የሚሰጥ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በአካል መድረስ ያለበት ሲሆን የኢንተርፕራይዙ ባለቤቶችን በአካል ማግኘት ካልተቻለ በመስሪያ ቦታው ላይ መለጠፍ አለበት፡፡ ቋሚ የመስሪያ አድራሻ የሌለው ኢንተርፕራይዝ ከሆነ ህዝብ በሚያታየው ቦታ እንዲሁም በወረዳው የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ መለጠፍ አለበት፡፡
   መ. ኢንተርፕራይዙ ተደራጅቶ ወደ ስራ ከገባ 1 ዓመት ያልሞላው ከሆነ እንደ ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ከሐምሌ 1 እስከ ጥቅምት 30 ድረስ ማደስ ያለበት ሆኖ ባሰራው የሂሳብ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት መሰረት በደረሰበት የዕድገት ደረጃ መሰጠት አለበት፡፡
3. አንድ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ሽግግር የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ ከተገኘ፣
   ሀ. ጀማሪ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ኢንተርፕራይዝ በቀጣዩ ዓመት መስፈርቱን አሟልቶ ከተገኘ እርከኑን ሳይጠብቅ እስከ አነስተኛ መብቃት የዕድገት ደረጃ ማግኘት ይችላል፡፡
   ለ. አንድ ኢንተርፕራይዝ ወደ ታዳጊ መካከለኛ የዕድገት ደረጃ የሚሸጋገረው ቢሮው በሚያስቀምጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በመስፈርቱ ተመዝኖ ሲያሟላ ዓመት ሳይጠብቅ ወደ ታዳጊ መካከለኛ መሸጋገር ይችላል፡፡
   ሐ. ኢንተርፕራይዙ የያዘው የዕድገት ደረጃ ጀማሪ ከሆነ የዕድገት ደረጃው በተሰጠው

በመስፈርቱ ሲመዘን ያገኘው ውጤት ወደ ታዳጊ መካከለኛ የሚያሸጋግረው ቢሆንም የሚሰጠው የዕድገት ደረጃ አነስተኛ መብቃት ሆኖ በቀጣይ ለመሸጋገር እንደማንኛውም ኢንተርፕራይዝ በወቅቱ ባመጣው መረጃ ተመዝኖ ለደረጃው የተሰጠውን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ ወደ ታዳጊ መካከለኛ መሸጋገር አለበት፡፡

መ. ኢንተርፕራይዙ የያዘው የዕድገት ደረጃ ከጀማሪ ውጭ ከሆነ ለዕድገት ደረጃ የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ ከተገኘ እርከኑን ሳይጠብቅ ወደ ማንኛውም የዕድገት ደረጃ መሸጋገር አለበት፡፡

4. አንድ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ እድሳት የሚሰጠው ለደረጃው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ያሟላውን የዕድገት ደረጃ ዓይነት ሲሆን በያዘው የዕድገት ደረጃ የቀጠለ ወይም ዝቅ ያለ ከሆነ፡-

ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ ሰርተፊኬቱ እድሳት ተደርጎለት ለሚመለከተው ደጋፊ ባለሙያና ባለድርሻ አካላት በደብዳቤ በማሳወቅ ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያገኝ መደረግ አለበት፡፡

ለ. በተሰጠው ተጨማሪ ድጋፍ ከፍ ወደ አለ የዕድገት ደረጃ ያልተሸጋገር ከሆነ ድጋፍ ከሰጠው አካል መረጃ በመሰብሰብ በቂ ድጋፍ ያልተደረገለት መሆኑ ሲረጋገጥ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬቱ መታደስ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ድጋፍ ከሰጠው አካል መረጃ በማሰባሰብ የተሰጠው ድጋፍ በቂ መሆኑ ከተረጋገጠ ከመንግስት ድጋፍ ማዕቀፍ ውጭ መሆን አለበት፡፡

ሐ. አምስተኛ ዓመት ላይ ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃውን ቢያሻሽልም ባያሻሽልም ወደ ታዳጊ መካከለኛ ካልተሸጋገረ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬቱ ተሰርዞ ከየትኛውም የጥቃቅንና አነስተኛ የድጋፍ ማዕቀፎች ውጪ መሆን አለበት፡፡

5. በስራ ላይ የሚገኙ ነባር ኢንተርፕራይዞች ከዚህ በፊት ምንም አይነት የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ያልተሰራላቸው ከሆነ እንዲሰራላቸው ሲደረግ በመስፈርቱ መሰረት ተመዝኖ በደረሱበት የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት መሰጠት አለበት ይሁንና የተሰጠው የዕድገት ደረጃ የሚያገለግለው እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ብቻ መሆን አለበት፡፡

6. ከተደራጁ ጀምሮ ምንም ዓይነት የዕድገት ደረጃ የሌላቸው ኢንተርፕራይዞች ካሉ የሁለት ወር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው የዕድገት ደረጃ ማውጣት ካልቻሉ ከድጋፍ ማዕቀፉ ውጭ መሆን አለባቸው፡፡

7. ወደ ታዳጊ መካከለኛ ለሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር የሚደረገው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ብቻ ሲሆን ኢንተርፕራይዞቹ በወቅቱ ወደ ታዳጊ መካከለኛ በአስፈጻሚ አካል ችግር ምክንያት ያልተሸጋገሩ ከሆነ ከዚህ በፊት የተሰጣቸው የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት ሳይመዘኑ እንዲታደስላቸው መደረግ አለበት፡፡ ይሁንና አንድ ኢንተርፕራይዝ የታዳጊ መካከለኛ የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት አንድ ጊዜ ከተሰጠው በኋላ በድጋሚ ሰርቲፊኬቱ መታደስ የለበትም፡፡

8. አንድ ኢንተርፕራይዝ በዕድገት ደረጃ መስፈርት ተመዝኖ ከመቶ ያገኘው ውጤት ወደ ሌላ የዕድገት ደረጃ ሊያሸጋግረው የሚችል ቢሆንም በመመሪያው ላይ የተቀመጠውን ዕደገት ደረጃ ሽግግር የሀብት መጠን ያላሟላ መሸጋገር የለበትም፣

## 9. የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት የሚሰጥባቸው የስራ ዘርፎች

1. የዕድገት ደረጃ የሚሰጣቸዉ በጥቃቅንና አነስተኛ አደረጃጀት መስፈርት አሟልተው ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ብቻ መሆን አለበት፡፡
2. የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት የሚሰጥባቸው የስራ ዘርፎች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ አደረጃጀት መመሪያ መሰረት በተቀመጡ የስራ ዓይነቶች ላይ ብቻ መሆን አለበት፡፡
3. የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት የሚሰጠው መስፈርቱን አሟልተው በንግድ ህጉ መሰረት ንግድ ፍቃድ ያወጡ ኢንተርፕይዞች ብቻ መሆን አለበት፡፡

## 10. የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት የማይሰጥባቸው የስራ ዘርፎች

ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ አደረጃጀቱ በህብረት ስራ ማህበር የሆነ እና በየትኛውም ዘርፍ ንግድ ፍቃድ ያላወጣ ከሆነ የዕድገት ደረጃ መሰጠት የለበትም፡፡

## 11. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ የዕድገት ደረጃ ዓይነቶች

1. ምስረታ ወይም ጀማሪ፤
2. ታዳጊ ወይም መስፋት፤
3. መብቃት፤

4. ታዳጊ መካከለኛ፤

12. **የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት የመለያ ቀለማት**

1. ለጥቃቅን ጀማሪ እና ለአነስተኛ ጀማሪ ኢንተርፕራይዝ **ነጭ** ሰርተፍኬት መሰጠት አለበት፡፡

2. ለጥቃቅን ታደጊ እና አነስተኛ ታዳጊ ኢንተርፕራይዝ **አረንጓዴ** ሰርተፍኬት መሰጠት አለበት፡፡

3. ለጥቃቅን መብቃት እና አነስተኛ መብቃት ኢንተርፕራይዝ **ቢጫ** ሰርተፍኬት መሰጠት አለበት፡፡

4. ለታደጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ **ሰማያዊ** ሰርተፍኬት መሰጠት አለበት፡፡

5. ከነበረበት የዕድገት ደረጃ በመስፍረቱ መሰረት ተመዝኖ ዝቅ ያለ የዕድገት ደረጃ ካገኘ **ቀይ** ሰርተፍኬት መሰጠት አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ አወሳሰንና እና ሽግግር መስፈርቶች

13. **ወደ ታዳጊ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ሊያሟሉዋቸው የሚገቡ መስፈርቶች**

1. **በሥራ ዕድል ፈጠራ**

ሀ. በኢንዱስትሪ ስራ ዘርፍ የተሰማራ የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ እስከ 3 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ የደሞወዝ ክፍያ ሰነድ የተከፈለ እስከ 2 ሰው መሆን አለበት፡፡

ለ. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ጊዜያዊ የሥራ ዕድል እስከ 2 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ 1 ሰው መሆን አለበት፡፡

ሐ. በኢንዱስትሪ ዘርፍም ሆነ በአገልግሎት የተሰማራ አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የሥራ ዕድል የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ 6 ሰዎች መሆን አለበት፡፡

መ. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በዓመት ውስጥ በጊዜያዊነት የፈጠረው የሥራ ዕድል እስከ 5 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ አስከ 4 ሰው መሆን አለበት፡፡

2. በሃብት መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤

ሀ. ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ከብር 50,001.00 እስከ ብር 75,000.00 መሆን አለበት::

ለ. ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ከብር 100,001.00 እስከ ብር 500,000.00 መሆን አለበት::

ሐ. ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 50% እና በላይ መሆን አለበት::

መ. ሳይበደሩ በራሳቸው ገንዘብ ወደ ስራ ለሚገቡ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 50 % እና በላይ ሆኖ ቋሚ ንብረት ኖሯቸው ለግብዓት የሚበደሩ ሙሉ በሙሉ ለስራው ማዋል አለበት፡፡

ሠ. የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲተር የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

3. በሃብት መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤

ሀ. ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ እሰከ ብር 40,000.00 መሆን አለበት::

ለ. ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ከብር 50,001.00 እሰከ ብር 200,000.00 መሆን አለበት::

ሐ. ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት የዋለው 20% እና በላይ መሆን አለበት::

መ. ሳይበደሩ በራሳቸው ገንዘብ ወደ ስራ ለሚገቡ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 20% እና በላይ ሆኖ ቋሚ ንብረት ኖሯቸው ለግብዓት የሚበደሩ ሙሉ በሙሉ ለስራው ማዋል አለበት፡፡

4. ትርፋማነት በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

ሀ. በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ ቢያንስ 10 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፡፡

ለ. ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት ወይም የቁጠባ

መጠን ከተጣራ ሃብት ከ20 % በላይ መሆን አለበት::

5. ትርፋማነት በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

ሀ. በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ ቢያንስ 10 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፡፡

ለ. ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት እና ወይም የቁጠባ መጠን ከተጣራ ሃብት ከ15% በላይ መሆን አለበት::

6. በገበያ መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤

ሀ. ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 75,000.00 እስከ ብር 100,000.00 መሆን አለበት::

ለ. ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 150,000.00 እስከ ብር 750,000.00 መሆን አለበት::

ሐ. ኢንተርፕራይዙ በ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ውስጥ በኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ ከ30% በላይ፣ በብረታ ብረትና እንጨት ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ቢያንስ ከ70% በላይ፣ በተቀሩት ዕድገት ተኮር ንዑሳን ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከ75% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት::

መ. ኢንተርፕራይዙ ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ ሦስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት::

ረ. ኢንተርፕራይዙ ለደረጃው በተዘጋጀ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ቢያንስ በ1 ዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜ የተሳተፈ መሆን አለበት::

7. በገበያ መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤

ሀ. ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን እስከ ብር 75,000.00 መሆን አለበት::

ለ. ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 75,001.00 እስከ ብር 200,000.00 መሆን አለበት::

ሐ. ከኢንተርፕራይዙ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ውስጥ ኢንተርፕራይዙ ከ70% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግሥት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት::

መ. ኢንተርፕራይዙ ምርትና አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ ቢያንስ ሦስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት::

8. **የኢንተርፕራይዙ ምርታማነት**

ሀ. በኢንዱስትሪም ሆነ በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ ምርታማነት ካለው ሙሉ የማምረት አገልግሎት የመስጠት አቅም ቢያንስ 50% በላይ መጠቀም አለበት፡፡

ለ. ከኢንተርፕራይዙ አባላት እና ወይም ቋሚ ሰራተኞች ቢያንስ 70% ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡

9. **በተቋማዊ አመራርና አደረጃጀት**

ሀ. ኢንተርፕራይዙ ዘመናዊ የሥራ አመራር ዘይቤ ተግባራዊ ማድረግ የጀመረ መሆን አለበት፡፡

ለ. ኢንተርፕራይዙ ለተሰማራበት የምርት እና ወይም የአገልግሎት ንግድ ሥራ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥራ ላይ ማዋል፣ የሂሳብ መግለጫ ማዘጋጀት ወይም ማቅረብ ኦዲት መደረግ አለበት::

ሐ የኢንተርፕራይዙ የማምረቻ ማዕከል አደረጃጃት የምርት ሂደትን የተከተለና ንጽህናው የተጠበቀ መሆን አለበት::

መ የኢንተርፕራይዙ አባላትን እና ሰራተኞችን የሥራ ደህንነት ለመጠበቅ የሥራ ልብስ እና  እንደ ንዑስ ዘርፉ ዓይነት የደህንነት መሣሪያዎች የተሟሉ መሆን አለበት::

ሠ. የኢንተርፕራይዙን ሥራ ለማስፋፋት የሚያስችል በጽሑፍ የተዘጋጀ የንግድ ዕቅድ መዘጋጀት  አለበት::

ረ. ከሌሎች ኢንተርፕራይዞች ጋር ስለ የንግድ  ሥራ ሃሳብ ለመለዋወጥም ይሁን የጋራ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስችል የንግድ ግንኙነት መፍጠር አለበት::

10. **በመንግሥታዊ ድጋፎች አጠቃቀም**

ሀ. የሚሰጠውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተግባር ላይ ያዋለ መሆን አለበት፡፡

ለ. የብድር ተጠቃሚ ከሆነ ያልተመለሰ ውዝፍ ብድር የሌለበት መሆን አለበት::

ሐ. የማምረቻ ማዕከል ተጠቃሚ ከሆነ የውል ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ መሆን አለበት::

መ. በመንግስት የሚሰጠውን የገበያ ትስስር በገባው ውል በአግባቡ እየሰራ ያለ ወይም ሰርቶ ያስረከበ መሆን አለበት፡፡

11. **በቴክኖሎጂ አጠቃቀም**

ሀ. ኢንተርፕራይዙ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማሻሻል በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶችና ሌሎች የቴክኖሎጂ ተቋማት የሚሰራጩ ተፈላጊና አዋጪ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ ለመሆን ቅድመ ዝግጅት ያደረገ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ አለበት::

ለ. ኢንተርፕራይዙ ከሚጠቀምባቸው የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች ውስጥ ቢያንስ 50% የአካባቢ ብክለት የማያስከትሉና ኢነርጂ ቆጣቢ መሆን አለበት::

12. **ግዴታን ስለመወጣት**

ሀ. ኢንተርፕራይዙ የሚጠበቅበትን ዓመታዊ ግብር መክፈል አለበት::

ለ. ኢንተርፕራይዙ ዓመታዊ የንግድ ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ አለበት::

ሐ. ኢንተርፕራይዙ የተሠጠውን የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት መመለስ አለበት፡፡

14. **ወደ መብቃት ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ሊያሟላቸው የሚገቡ መስፈርቶች**

1. **በሥራ ዕድል ፈጠራ**

ሀ. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የሥራ ዕድል የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ እስከ 5 ሰዎችን ያሰማራ ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ እስከ 5 ሰው መሆን አለበት፡፡

ለ. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ጊዜያዊ የሥራ ዕድል እስከ 3 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ እስከ 2 ሰው መሆን አለበት፡፡

ሐ. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የሥራ ዕድል የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ ከ6 እስከ 15 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ6 እስከ 15 ሰው መሆን አለበት፡፡

መ. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በዓመት ውስጥ በጊዜያዊነት የፈጠረው የሥራ ዕድል ከ 3 እስከ 15 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ2 እስከ 15 ሰው መሆን አለበት፡፡

2. **በሃብት መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤**

ሀ. ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሀብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ከብር 75,001.00 እስከ ብር 100,000.00 መሆን አለበት::

ለ. ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሀብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ከብር 500,001.00 እስከ ብር 1,500,000.00 መሆን አለበት::

ሐ. ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘውገንዘብ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 50%እና በላይ መሆን አለበት::

መ. ሳይበደሩ በራሳቸው ገንዘብ ወደ ስራ ለሚገቡ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 50 % እና በላይ ሆኖ ቋሚ ንብረት ኖሯቸው ለግብዓት የሚበደሩ ሙሉ በሙሉ ለስራው ማዋል አለበት፡፡

ሠ. የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲተር የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

3. **በሃብት መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤**

ሀ. ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ከብር 40,001 እስከ ብር 50,000.00 መሆን አለበት::

ለ. ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሀብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ከብር 50,001.00 እሰከ ብር 500,000.00 መሆን አለበት::

ሐ. ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት የዋለው 20% እና በላይ መሆን አለበት::

መ. ሳይበደሩ በራሳቸው ገንዘብ ወደ ስራ ለሚገቡ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 20 % እና በላይ ሲሆን ቋሚ ንብረት ኖሯቸው ለግብዓት የሚበደሩ ሙሉ በሙሉ ለስራው ማዋል አለበት፡፡

ሠ. የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲተር የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

4. **ትርፋማነት በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች**

ሀ. በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ 20 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፡፡

ለ. ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት እና ወይም የቁጠባ መጠን ከተጣራ ሃብት ከ30% በላይ መሆን አለበት::

5. **ትርፋማነት በአገልግት ዘርፍ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች**

ሀ. በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ 20 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፡፡

ለ. ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት እና ወይም የቁጠባ መጠን ከተጣራ ሃብት ከ20% በላይ መሆን አለበት::

6. **በገበያ መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤**

ሀ. ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ በ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 75,000.00 እስከ ብር 100,000.00 መሆን አለበት::

ለ. ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 500,001.00 እስከ ብር 1,500,000.00 መሆን አለበት::

ሐ. ከኢንተርፕራይዙ በ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ውስጥ በኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ ከ35% በላይ በብረታ ብረትና እንጨት ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ ከ75% በላይ በቀሩት ዕድገት ተኮር ንዑሳን ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከ80% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት::

መ. ኢንተርፕራይዙ ለሌሎች ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በንዑስ ኮንትራት በ1 ዓመት ቢያንስ 2 ጊዜ የገበያ ትስስር የፈጠረ መሆን አለበት::

ሠ. ኢንተርፕራይዙ ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ አምስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት::

ረ. ኢንተርፕራይዙ ለደረጃው በተዘጋጀ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ቢያንስ በዓመት ሶስት ጊዜ የተሳተፈ መሆን አለበት::

7. በገበያ መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤

ሀ. ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 50,001.00 እስከ ብር 75,000 መሆን አለበት::

ለ. ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ 1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 200,001.00 እስከ ብር 750,000.00 መሆን አለበት፡፡

ሐ. ከኢንተርፕራይዙ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ውስጥ ከ85% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት::

ሠ. ኢንተርፕራይዙ ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ አምስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት::

8. የኢንተርፕራይዙ ምርታማነት

ሀ. በኢንዱስትሪም ሆነ በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ ምርታማነት ካለው ሙሉ የማምረት አቅም ቢያንስ 70% በላይ መጠቀም አለበት፡፡

ለ. ኢንተርፕራይዙ ለሚያመርታቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ዘመናዊ የስራ አመራርን የተከተለ የጥራት ቁጥጥር ስርዓት የዘረጋ መሆን አለበት::

ሐ. ለገቢ ወይም ለወጪ ምርቶች የሚውሉ ግብዓቶችን ወይም ገቢ ምርቶችን የሚተካ ወይም ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ማምረት መቻል አለበት::

መ. ከኢንተርፕራይዙ አባላት እና ወይም ቋሚ ሰራተኞች ቢያንስ 75% ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መኖር አለበት::

9. በተቋማዊ አመራርና አደረጃጀት

ሀ. ኢንተርፕራይዙ ዘመናዊ የሥራ አመራር ዘይቤ ተግባራዊ ያደረገና ስትራቴጂክ ዕቅድ መኖር አለበት፡፡

ለ. ኢንተርፕራይዙ ለተሰማራበት የምርት እና ወይም የአገልግሎት ንግድ ሥራ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥራ ላይ ማዋል እና ኦዲት ማስደረግ አለበት፡፡

ሐ. የኢንተርፕራይዙ አባላትን እና ሰራተኞችን የሥራ ደህንነት ለመጠበቅ የሥራ ልብስ እና እንደ ንውስ ዘርፉ ዓይነት የደህንነት መሣሪያዎች የተሟሉ መሆን አለበት::

መ. የኢንተርፕራይዙን ሥራ ለማስፋፋት የሚያስችል በጽሑፍ የተዘጋጀ የንግድ እቅድ መዘጋጀት አለበት::

ሠ ከሌሎች ኢንተርፕራይዞች ጋር ስለ ቢዝነስ ሥራ ሃሳብ ለመለዋወጥም ይሁን የጋራ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስችል የንግድ ግንኙነት መፍጠር አለበት::

10. **በመንግስታዊ ድጋፎች አጠቃቀም**

ሀ. የሚሰጠውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተግባር ላይ አውሎ ተጨባጭ ለውጥ ያመጣና የአሠራሩን ለሌሎች ተሞክሮውን ለማስተላለፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡

ለ. ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ጋር በትብብርና በኩባንያ ውስጥ ስልጠና የሚሳተፍ መሆን አለበት፤

ሐ. ተደጋጋሚ የብድር ተጠቃሚ ሆኖ ያልተመለሰ ውዝፍ ብድር የሌለበት መሆን አለበት:

መ. የመስሪያ ቦታ ተጠቃሚ ከሆነ የውል ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ መሆን አለበት::

ሠ. በመንግስት የሚሰጠውን የገበያ ትስስር በገባው ውል በአግባቡ እየሰራ ያለ ወይም ሰርቶ ያስረከበ መሆን አለበት፡፡

ረ የመስሪያ ቦታ ተጠቃሚ ከሆነ የኪራይ ውዝፍ ዕዳ የሌለበትና ከማዕከሉ ከመውጣቱ በፊት አስፈላጊውን የፋይናንስና የማምረቻ ቦታ ቅድመ ዝግጅት ያደረገ መሆን አለበት::

11. **በቴክኖሎጂ አጠቃቀም**

ሀ. ኢንተርፕራይዙ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማሻሻል በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶችና ሌሎች የቴክኖሎጂ ተቋማት የሚሰራጩ ተፈላጊና አዋጪ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ መሆን አለበት::

ለ. የምርትና አገልግሎት ጥራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ወቅታዊና የተሻሻለ አሠራር ተጠቃሚ መሆን አለበት::

ሐ. ኢንተርፕራይዙ ከሚጠቀምባቸው የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች ውስጥ ቢያንስ 75% የአካባቢ ብክለት የማያስከትሉና ኢነርጂ ቆጣቢ መሆን አለበት::

12. **ግዴታን ስለመወጣት**

ሀ. ኢንተርፕራይዙ የሚጠበቅበትን የ1 ዓመት የገቢ ግብር መክፈል አለበት::

ለ. ኢንተርፕራይዙ ዓመታዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ አለበት::

ሐ. ኢንተርፕራይዙ የተሠጠውን የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት መመለስ አለበት፡፡

15. **ወደ ታዳጊ መካከለኛ ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ሊያሟሉዋቸው የሚገቡ መስፈርቶች**

1. **በስራ ዕድል ፈጠራ**

ሀ. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የሥራ ዕድል የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ ከ30 በላይ ሆኖ በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ20 በላይ መሆን አለበት፡፡

ለ. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ በዓመት ውስጥ በጊዜያዊነት የፈጠረው የሥራ ዕድል ከ20 በላይ ሰዎች ሆኖ በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ15 በላይ መሆን አለበት፡፡

2. **በሃብት መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤**

ሀ. ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ከብር 1.5 ሚሊዮን በላይ መሆን አለበት::

ለ. ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 70% እና በላይ መሆን አለበት::

ሐ. የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲት የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

3. **በሃብት መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ**

ሀ. ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ከብር 500,000.00 በላይ መሆን አለበት::

ለ. ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 40% እና በላይ መሆን አለበት::

ሐ. የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲት የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

4. **ትርፋማነት በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች**

ሀ. በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ እስከ 30 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፡፡

ለ. ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት እና ወይም የቁጠባ መጠን ከተጣራ ሃብት ከ50% በላይ መሆን አለበት::

5. **ትርፋማነት በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች**

ሀ. በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ እስከ 30 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፡፡

ለ. ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት እና ወይም የቁጠባ መጠን ከተጣራ ሃብት ከ30% በላይ መሆን አለበት::

6. **በገበያ መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤**

ሀ. የኢንተርፕራይዙ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 4500,000.00 በላይ መሆን አለበት::

ለ. ከኢንተርፕራይዙ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ውስጥ በኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ 50% በላይ በብረታ ብረትና

እንጨት ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ ከ80% በላይ እና በተቀሩት ዕድገት ተኮር ንዑሳን ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከ90% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት::

ሐ. ኢንተርፕራይዙ ለሌሎች ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በንዑስ ኮንትራት በ1 ዓመት ቢያንስ 5 ጊዜ የገበያ ትስስር የፈጠረ መሆን አለበት::

መ. ኢንተርፕራይዙ ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ አምስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት::

ሠ. ኢንተርፕራይዙ ለደረጃው በተዘጋጀ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ቢያንስ በ1 ዓመት ሁለት ጊዜ የተሳተፈ መሆን አለበት::

7. **በገበያ መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤**

ሀ. ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ከብር 1500,000.00 መሆን አለበት::

ለ. ከኢንተርፕራይዙ ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ውስጥ ከ90% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት::

ሐ. ኢንተርፕራይዙ ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ አምስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት::

8. **የኢንተርፕራይዙ ምርታማነት**

ሀ. በኢንዱስትሪም ሆነ በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ ምርታማነት ካለው ሙሉ የማምረት አቅም ቢያንስ 85 % በላይ መጠቀም አለበት፡፡

ለ. ኢንተርፕራይዙ ለሚያመርታቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ዘመናዊ የስራ አመራርን የተከተለ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋ መሆን አለበት::

ሐ. ለገቢ ወይም ለወጪ ምርቶች የሚውሉ ግብዓቶችን ወይም ገቢ ምርቶችን የሚተካ ወይም ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ማምረት መቻል አለበት::

መ. ከኢንተርፕራይዙ አባላት እና ወይም ቋሚ ሰራተኞች ቢያንስ 90% ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መኖር አለበት፡፡

9. በተቋማዊ አመራርና አደረጃጀት

ሀ. ኢንተርፕራይዙ ዘመናዊ የስራ አመራር ዘይቤ ተግባራዊ ያደረገና ስትራቴጂክ ዕቅድ መኖር አለበት፡፡

ለ ኢንተርፕራይዙ ለተሰማራበት የምርት እና ወይም የአገልግሎት ንግድ ሥራ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥራ ላይ ማዋል እና ኦዲት ማስደረግ አለበት፡፡

ሐ. የኢንተርፕራይዙ አባላትን እና ሰራተኞችን የስራ ደህንነት ለመጠበቅ የሥራ ልብስ እና እንደ ንዑስ ዘርፉ ዓይነት የደህንነት መሣሪያዎች የተሟሉ መሆን አለበት::

መ. የኢንተርፕራይዙን ሥራ ሽግግር የሚያሳይ በጽሑፍ የተዘጋጀ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል መዘጋጀት አለበት::

ሠ. ከሌሎች ኢንተርፕራይዞች ጋር ስለ ቢዝነስ ሥራ ሃሳብ ለመለዋወጥም ይሁን የጋራ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስችል የንግድ ግንኙነት መፍጠር አለበት::

10. በመንግሥታዊ ድጋፎች አጠቃቀም

ሀ. የሚሰጠውን ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተግባር ላይ አውሎ ተጨባጭ ለውጥ ያመጣና የአሠራሩን ሌሎች ተሞክሮውን ለማስተላለፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡

ለ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ጋር በትብብርና በኩባንያ ውስጥ ስልጠና የተሳተፈ መሆን አለበት፡፡

ሐ .ተደጋጋሚ የብድር ተጠቃሚ ሆኖ ያልተመለሰ ውዝፍ ብድር የሌለበት መሆን አለበት::

መ. የማምረቻ ማዕከል ተጠቃሚ ከሆነ የውል ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ መሆን አለበት::

ሠ. በመንግስት የሚሰጠውን የገበያ ትስስር በገባው ውል በአግባቡ እየሰራ ያለ ወይም ሰርቶ ያስረከበ መሆን አለበት፡፡

ረ. ወደ ኢንዱስትሪ ዞን ለመግባት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ያጠናቀቀ መሆን አለበት፡፡

ሰ. ከንግድና ልማት ባንኮች ለመበደር የሚያስችል የብድር ዋስትና ያዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

11. **በቴክኖሎጂ አጠቃቀም**

ሀ. ኢንተርፕራይዙ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማሻሻል በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶችና ሌሎች የቴክኖሎጂ ተቋማት የሚሰራጩ ተፈላጊና አዋጪ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ መሆን አለበት፡፡

ለ. የምርትና አገልግሎት ጥራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ወቅታዊና የተሻሻለ አሠራር ተጠቃሚ መሆን አለበት፡፡

ሐ. ኢንተርፕራይዙ ከሚጠቀምባቸው የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች ውስጥ ቢያንስ 85% የአካባቢ ብክለት የማያስከትሉና ኢነርጂ ቆጣቢ መሆን አለበት::

12. **ግዴታን ስለመወጣት**

ሀ. ኢንተርፕራይዙ የሚጠበቅበትን ዓመታዊ የገቢ ግብር መክፈል አለበት፡፡

ለ. ኢንተርፕራይዙ ዓመታዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ አለበት፡፡

ሐ. ኢንተርፕራይዙ የተሠጠውን የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት መመለስ አለበት፡፡

16. **ወደ ታዳጊ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የመሸጋገር ሂደት**

ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የሚደረገው ሽግግር ዘርፍን፣ ካፒታልንና የተፈጠረን የስራ ዕድል መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ በዚህም መሰረት፡

1. በኢንዱስትሪ ዘርፍ አባላቱን ጨምሮ ኢንተርፕራይዙ የፈጠረው ቋሚ የስራ ዕድል ከ30 ሰው በላይ፣ ጊዜያዊ የስራ ዕድል ከ20 ሰው በላይ ሆኖ ካፒታሉ ከብር 1.5 ሚሊዮን በላይ ሲሆንና በማስረጃ መረጋገጥ አለበት፡፡
2. በአገልግሎት ዘርፍ አባላቱን ጨምሮ ኢንተርፕራይዙ የፈጠረው ቋሚ የስራ ዕድል ከ20 ሰው በላይ ፣ጊዜያዊ የስራ ዕድል ከ15 በላይ ሆኖ ካፒታሉ ከብር 500,000.00 አምስት መቶ ሺ በላይ ሲሆን በማስረጃ መረጋገጥ አለበት፡፡

3. ወደ ታዳጊ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ለደረጃው የሚጠበቀውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኙ የዕድገት ደረጃና ሽግግር ሂደት፡-

ሀ. በወረዳ ደረጃ በባለሙያ የተለየውን የኢንተርፕራይዞች መረጃ በጽ/ቤት ፕሮሰስ ካውስል በማጸደቅ የጸደቀበትን ቃለ ጉባኤ በጽ/ቤት ሃላፊው ተረጋግጦ ለክፍለ ከተማው የስራ ዕድል ፈጠራ እና ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት መላክ አለበት፡፡

ለ. የክፍለ ከተማው ደረጃ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ባለሙያ ከወረዳ የደረሰውን መረጃ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ለፕሮሰስ ካውስል አቅረቦ በማጸደቅ የጸደቀበትን ቃለ ጉባኤ በጽ/ቤት ሃላፊው ተረጋግጦ ለስራ ዕድል ፈጠራ እና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ መላክ አለበት፡፡

ሐ. ከየክፍለ ከተሞች የደረሰውን መረጃ ትክክለኛነቱን በስራ ሂደቱ በማረጋገጥ ለፕሮሰስ ካውስል አቅረቦ በማጸደቅ ኢንተርፕራይዞች እውቅና ኢንዲያገኙ ማደረግ አለበት፡፡

መ. የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለዉ የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲት የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር

17. የቢሮ ስልጣንና ተግባር

1. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ስትራቴጅውን መሰረት በማድረግ የዕድገት ደረጃ ማኑዋሎች እና መመሪያዎች ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል አፈጻጸምን ይከታተላል፡፡
2. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ስትራቴጅውን መሰረት በማድረግ የዕድገት ደረጃ ማኑዋሎች እና መመሪያዎች ላይ ግንዛቤ ማሰጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡
3. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የወጡ የድጋፍ ማዕቀፎች አፈፃፀም የኢንተርፕራይዞች የዕደገት ደረጃን መሰረት ያደረገ መሆኑን ክትትል በማድረግ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

4. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የድጋፍ ማዕቀፎችን በዕደገት ደረጃቸውና በተቀመጠው የድጋፍ አይነት እና መጠን መሰረት ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን ይከታተላል፣ የጠራ መረጃ ይይዛል፣ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

5. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መስፍረቱን አሟልተው ሲገኙ ወደ ታደጊ መካከለኛ የዕድገት ደረጃ የዕውቅና ሰርተፊኬት በመስጠት ያሸጋግራል፡ ለሚመለከታቸው ተቋማት መረጃውን ይሰጣል፡፡

6. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከጀማሪ እስከ መብቃት የተሰጣቸው የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት በመመሪያ መሰረት መሆኑን ይከታተላል፡፡

7. በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ እና የሽግግር ሂደት መሰረት የሚቀርቡ ቅሬታ እና አቤቱታ በቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት መሰረት እንዲስተናገዱ ያደርጋል፡ ይከታተላል፡፡

8. የዕድገት ደረጃን በተመለከተ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት ይፈታል እንዲፈታ ያደርጋል፡፡

9. የዕድገት ደረጃ የተሰጣቸውን ኢንተርፕራይዞች መረጃ አጠናክሮ ይይዛል፤ መረጃውን ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡

10. በመደበኛ ድጋፍ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ማድረግ ያልቻሉ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ተጨማሪ ድጋፍ እንዲደረግላቸው መረጃውን በማደራጀት ለባለድርሻ አካላት ይሰጣል፡፡

11. ባለድርሻ አካላት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡትን ድጋፍ የዕድገት ደረጃቸውን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይከታተላል፤ ድጋፍ ይሰጠል፡፡

## 18. የክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የዕድገት ደረጃ ማኑዋሎች እና መመሪያዎች እንዲዘጋጁ ግብዓት ይሰጣል፤ የወጡትን ተግባራዊ ያደርጋል፤ ይከታተላል፡፡

2. ለባለሙያዎች፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ባለድርሻ አካላት ስትራቴጅውን መሰረት በማድረግ የዕድገት ደረጃ ማኑዋሎች እና መመሪያዎች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

3. ለኢንተርፕራይዞች እየተሰጠ ያለው የድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም የኢንተርፕራይዞችን የዕደገት ደረጃ መሰረት ያደረገ መሆኑን ክትትል በማድረግ ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፡፡

4. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መስፍረቱን አሟልተው ሲገኙ ወደ ታዳጊ መካከለኛ የዕድገት ደረጃ የሚሸጋገሩትን መረጃ አጠናክሮ በፕሮሰስ ካውንስል በማስወሰን ለቢሮ ይልካል፡፡

5. ለጀማሪ፣ ለታዳጊ እና መብቃት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተሰጣቸው የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት በመመሪያ መሰረት መሰራቱን ይከታተላል፡፡ ድጋፍ ያደርጋል፤

6. በዕድገት ደረጃ እና ሽግግር አሰራር ላይ የሚቀርቡ ቅሬታ እና አቤቱታዎች በቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መሰረት እንዲስተናገዱ ያደርጋል፡ ይከታተላል፡፡

8. የዕድገት ደረጃን በሚመለከት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት ችግሮቹ እንዲፈቱ ያደርጋል፣ ይከታተላል፡፡ ችግሩ የመመሪያ ከሆነ ለከተማው የጥናቱን ውጤት ከነመፍትሄው ያመላክታል፡፡

9. የዕድገት ደረጃ የተሰጣቸውን ኢንተርፕራይዞች መረጃ አጠናቅሮ ይይዛል፤ መረጃውን አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡

10. በመደበኛ ድጋፍ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ማድረግ ያልቻሉ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ተጨማሪ ድጋፍ እንዲደረግላቸው መረጃውን በማደራጀት ለሚመለከተው ፈጻሚና ባለድርሻ አካል ይሰጣል፡፡

11. የሚመለከታቸው ፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡትን ድጋፍ የኢንተርፕራዞቹን የዕድገት ደረጃ መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይከታተላል፡ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

**19. የወረዳ ስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ስልጣንና ተግባር፡-**

1. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ስትራቴጅውን መሰረት በማድረግ የዕድገት ደረጃ ማኑዋሎች እና መመሪያዎች እንዲዘጋጁ ግብዓት ይሰጣል፤ የወጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

2. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ስትራቴጅውን መሰረት በማድረግ የዕድገት ደረጃ ማኑዋሎች እና መመሪያዎች ላይ የግንዛቤ ማሰጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፣

3. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ የድጋፍ ማዕቀፎች አፈፃፀም የኢንተርፕራይዞች የዕደገት ደረጃን መሰረት ያደረገ መሆኑን ክትትል በማድረግ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

4. ወደ ታደጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ለመሸጋገር መስፈርቱን ያሟሉ ኢንተርፕራይዞችን መረጃ አጠናክሮና አደራጅቶ በፕሮሰስ ካውንስል በማስወሰን ለክፍለ ከተማ ይልካል፡፡

5. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጀማሪ፣ ታደጊ እና መብቃት የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት በመመሪያ መሰረት ይሰጣል፡፡

6. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ እና የሽግግር ሂደት መሰረት የሚቀርቡ ቅሬታ እና አቤቱታ በቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መሰረት እንዲስተናገዱ ያደርጋል፡፡

7. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ በሚመለከት የሚያጋጥሙ ችግሮች በጥናት እንዲፈቱ ለግብዓት የሚሆን መረጃ ይሰበስባል፡፡

8. በመደበኛ ድጋፍ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ማድረግ ያልቻሉ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ተጨማሪ ድጋፍ እንዲደረግላቸው መረጃውን በማደራጀት ለፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ይሰጣል፡፡

10. ባለድርሻ አካላት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡትን ድጋፍ የዕድገት ደረጃቸውን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይከታተላል፡ ድጋፍ ይሰጠል፡፡

## ክፍል አምስት

## መብትና ግዴታዎች

20. **የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መብት፡-**

11. በዕድገት ደረጃ አሰጣጥና ሽግግር አሰራር ሥርዓት መሰረት ለደረሱበት የዕድገት ደረጃ መስፈርቱን አሟልቶ ሲገኝ የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት ማግኘት ይችላል፡፡

2. በተሰጣቸው የዕድገት ደረጃ እውቅና ሰርተፊኬት መሰረት በደረሰበት ደረጃ የሚሰጠውን ድጋፍ ማግኘት ይችላል፡፡

3. በዕድገት ደረጃ አሰጣጥ እና ሽግግር እንዲሁም የዕድገት ደረጃን መሰረት ያደረገ ድጋፍ

አሰጣጥ ላይ ቅሬታና አቤቱታ በአሰራር ሥርዓት መሰረት ማቅረብ እና ምላሽ ማግኘት ይችላል፡፡

21. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ግዴታ፡-

1. ኢንተርፕራይዙ ለዕድገት ደረጃ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች እና መረጃዎች በማሟላት በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ሳይደብቅ በግልጽ መስጠት አለበት፡፡

2. ኢንተርፕራይዙ የተሰጠውን የዕድገት ደረጃ በዓመቱ ወቅቱን ጠብቆ ማሳደስ አለበት፡፡

3. የሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎችን በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል አለበት፡፡

4. የዕድገት ደረጃ ሽግግር ሲያደርግ በፊት የተሰጠውን የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት መመለስ አለበት፡፡

5. የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት የጠፋባቸው ለአካባቢው ፖሊስ አመልክቶ የጠፋበት መሆኑን አስመስክሮ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

22. የዘርፉ አመራር እና ፈጻሚ መብት፡-

1. የዕድገት ደረጃ ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎችን ከኢንተርፕራይዙና ከሌሎች አጋዥ ሴክተሮች መጠየቅና መውሰድ ይችላል፡፡

2. የተሰጡ ድጋፎች የዕድገት ደረጃን መሰረት ያደረጉ ስለመሆኑ የመጠየቅና ማረጋገጥ ይችላል፡፡

23. የዘርፉ አመራር እና ፈጻሚ ግዴታ፡-

1. በዕድገት ደረጃ መስፈርት እና በአሰራሩ ዙሪያ ለኢንተርፕራይዞች መረጃ እና ግንዛቤ መስጠት አለበት፡፡

2. የሚሰጡ የዕድገት ደረጃ እና ድጋፎች የአሰራር ሥርዓቱን የተከተለ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

3. ኢንተርፕራይዞች በመስፈርቶችና ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ መሰረት የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ ተሰቷቸው በየዓመቱ ሰርቲፊኬት የማደስ እና የበፊቱን የተሰጣቸውን ሰርቲፊኬት እንዲመልሱ መደረግ አለበት፡፡

4. ለኢንተርፕራይዞች የተሰጣቸውን የዕድገት ደረጃ መረጃ በዓይነት፣ በስራ ዘርፍ፣ በዕድገት ደረጃ አደራጅቶ የመያዝ፤ የመተንተን እና የማሰራጨት ግዴታ አለበት፡፡

## 24. የተጠያቂነት ሥርዓት

### 1. ፈጻሚ አካል

የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ መስፈርት ሳይከተል የዕድገት ደረጃ የሰጠ ወይም ያደሰ ወይም ድጋፍ የሰጠ አመራር ወይም ፈፃሚ በህግ ተጠያቂ መሆን አለበት፡፡

### 2. ኢንተርፕራይዝ

የኢንተርፕራይዙን የዕድገት ደረጃ ለመስራት መረጃ ሲሰበሰብ የተሻለ የዕድገት ደረጃ ለማግኘት ወይም የዕድገት ደረጃውን ዝቅ ለማድረግ ወይም ከፍ ያለ ደረጃ ላለመወሰድ ሲባል የተሳሳተ መረጃ የሠጠ ወይም ሐሰተኛ ማስረጃ ያቀረበ ኢንተርፕራይዝ እንደየ ጥፋቱ ደረጃ አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ በህግ ተጠያቂ መሆን አለበት፡፡

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ጉዳዮች

## 25. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው አሰራሮች

ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ማንኛውም መመሪያዎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዬች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ፡፡

## 26. የተሻሩ መመሪያዎች

ከዚህ ቀደም የነበሩ የዕድገት ደረጃ አወሳሰን እና ሽግግር አፈጻጸም መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## 37. መመሪያ ስለማሻሻል

ቢሮው እንደ አስፈላጊነቱ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 28. መመሪያው ስለሚጸናበት ሁኔታ

ይህ መመሪያ ከዛሬ ግንቦት -- ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ግንቦት/2011 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

አባሪ

አባሪ 1:- የኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግር መስፈርቶችና መመዘኛ ነጥቦች

| ተ.ቁ | የሽግግር መስፈርቶች | ከኢንተርፕራይዞች ሽግግር ደረጃዎች አንፃር ለመስፈርቶች የተሰጠ ነጥብ በመቶኛ/%/ | | | መስፈርቶቹ የሚለኩባቸው ስልቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ወደ ታዳጊ | ወደ መብቃት | ወደ ታዳጊ መካከለኛ | |
| 1 | **ሥራ ዕድል ፈጠራ** | **20** | **25** | **25** | ፔይ ሮልን መነሻ በማድረግ በቁጥር |
| 1.1 | ቋሚ የሥራ ዕድል | 15 | 20 | 20 | |
| 1.2 | ጊዜያዊ የሥራ ዕድል | 5 | 5 | 5 | |
| 2 | **የሀብት መጠን** | **30** | **35** | **35** | የተረጋጠ የኦዲት ሪፖርት ወይም የተረጋገጠ የሀብትና ዕዳ መግለጫ |
| 2.1 | ጠቅላለ የሀብት መጠን | 15 | 15 | 20 | |
| 2.2 | በብድር ከተገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት የዋለ መጠን | 15 | 20 | 15 | |
| 3 | **ትርፋማነት** | **15** | **10** | **10** | • የትርፍና ኪሰራ መግለጫ<br>• የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት ወይም የተረጋገጠ የሀብትና ዕዳ መግለጫ |
| 3.1 | ተከታታይና ተመጣጣኝ ትርፍ ማስመዝገብ | 5 | 3 | 5 | |
| 3.2 | ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋት እና ወይም ለቁጠባ የዋለ ገንዘብ መጠን | 10 | 7 | 5 | |
| 4 | **የገበያ መጠን** | **8** | **8** | **10** | |
| 4.1 | ዓመታዊ የሽያጭ መጠን | 2 | 2 | 3 | የሽያጭ መረጃ በማየት |
| 4.2 | ከመንግስት ውጪ የተፈጠረ የገበያ ትስስር መጠን | 2 | 3 | 2 | የሽያጭ መረጃ በማየት |
| 4.3 | በንዑስ ኮንትራት ለሌሎች ኢንተርፕራይዞች በዓመት የፈጠረው የገበያ ትስስር ብዛት | 2 | 1 | 3 | ውል በማየት |
| 4.4 | ምርት ወይም አገልግሎት ለማስተዋወቅ የተጠቀመባቸው ዘዴዎች | 1 | 1 | 1 | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 4.5 | የኤግዚቪሽንና ባዛር ተሳትፎ ብዛት | 1 | 1 | 1 | በተሳትፎ የምስክር ወረቀት |
| 5 | **ምርታማነት** | **7** | **4** | **5** | |
| 5.1 | ካለው ሙሉ የማምረት አቅም የተጠቀመው | 3 | 2 | 3 | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 5.2 | የብቃት ማረጋጫ | 4 | 2 | 2 | የምስክር ወረቀት |
| 6 | **በመንግስታዊ ድጋፎች አጠቃቀም** | **6** | **5** | **5** | በአንድ ማዕከል አገልግሎት ሰራተኞች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 7 | **የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም** | **5** | **5** | **5** | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 8 | **ተቋማዊ አመራርና አደረጃጀት** | **5** | **4** | **3** | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 9 | **ግዴታን ስለመወጣት** | **4** | **4** | **2** | |
| 9.1 | ዓመታዊ የገቢ ግብር መክፈል | 2 | 3 | 1 | የገቢ ግብር ክሊራንስ |
| 9.2 | የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ማሳደስ | 2 | 1 | 1 | የታደሰ የምዝገባና የንግድ ፈቃድ |
| | **ድምር** | 100% | 100% | 100% | |

**ማስታወሻ፦**

(1ኛ) የኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግር የሚፈፀመው ለየዕድገት ደረጃው በድምር በመቶኛ/%/ ከተቀመጠው ወደ ታዳጊ ≥ 75% ሲያገኙ& ወደ መብቃት ≥ 80% ሲያገኙ& እና ወደ ታዳጊ መካከለኛ ≥ 85% ሲያገኙ ይሆናል::

(2ኛ) ከላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሟላ ሙሉ ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን ከከፍተኛው ነጥብ ቀጥሎ ወደታች የሚገኝ የነጥብ ውጤት የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ ስሌት በመስራት ይቀመጣል::

(3ኛ) የመንግስታዊ ድጋፎች ተጠቃሚ ያልሆነ ኢንተርፕራይዝ በዕድገት ደረጃ ሽግግር ወቅት ለዚህ የተቀመጠውን ሙሉ ነጥብ ያገኛል::

አባሪ 2፡

| የኢንተርፕራይዙ ዓይነት | የተሰማራበት ዘርፍ | የኢንተርፕራይዙ ሃብት መጠን | ገና ከጅምሩ ኢንተርፕራይዙ የሚፈረጀረበት የዕድገት ደረጃ | በሌሎች መመዘኛ መስፈርቶች ተመዝኖ ኢንተርፕራይዙ ከመቶ ያገኘው ነጥብ | ለኢንተርፕራይዙ የሚሰጠው የመጨረሻ የዕድገት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ | አገልግሎት | እስከ ብር 40,000 | ታዳጊ | ከ 75% በታች | ጀማሪ |
| | | | | ከ 75% በላይ | ታዳጊ |
| | | ከብር 40,001 እስከ ብር 50,000 | መብቃት | ከ 85% በታች | ታዳጊ |
| | | | | 85% እና በላይ | መብቃት |
| | ኢንዱስትሪ | ከብር 50,000 እስከ 75,000 | ታዳጊ | ከ 75% በታች | ጀማሪ |
| | | | | ከ 75% በላይ | ታዳጊ |
| | | ከብር 75,001 እስከ 100,000 | መብቃት | ከ 85% በታች | ታዳጊ |
| | | | | 85% እና በላይ | መብቃት |
| አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ | አገልግሎት | ከብር 50,000 እሰከ ብር 200,000 | ታዳጊ | ከ 75% በታች | ጀማሪ |
| | | | | ከ 75% በላይ | ታዳጊ |
| | | ከብር 200,001 እሰከ ብር 500,000 | መብቃት | ከ 85% በታች | ታዳጊ |
| | | | | ከ 85% በላይ | መብቃት |
| | | ከብር 500,000 በላይ | ታዳጊ መካከለኛ | ከ 85% በታች | መብቃት |
| | | | | 85% እና በላይ | ታዳጊ መካከለኛ |
| | ኢንዱስትሪ | ከብር 100,000 እስከ 500,000 | ታዳጊ | ከ 75% በታች | ጀማሪ |
| | | | | ከ 75% በላይ | ታዳጊ |
| | | ከብር 500,001 እስከ 1,500,000 | መብቃት | ከ 85% በታች | ታዳጊ |
| | | | | ከ 85% በላይ | መብቃት |
| | | ከብር 1.5 ሚልዮን በላይ | ታዳጊ መካከለኛ | 85% እና በታች | መብቃት |
| | | | | 85% እና በላይ | ታዳጊ መካከለኛ |